# ትምህርት 26

1. ለፈርዖን ሕልም ያሳየው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

2. እግዚአብሔር ለፈርዖን ያሳየው የመጀመሪያው ሕልም ምን ነበረ?

ሀ- ሰባት የከሱ ላሞች ሰባት ወፋፍራም ላሞችን ሲውጡአቸው ተመለከተ።

3. እግዚአብሔር ለፈርዖን ያሳየው ሁለተኛው ሕልም ምን ነበር?

ሀ- ሰባት ቀጫጭን የእሸት ዘለላዎች ሰባት ወፋፍራም የእሸት ዘለላዎችን ሲውጡአቸው ተመለከተ።

4. የፈርዖንን የሕልም ፍቺ ለዮሴፍ የሰጠው ማን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

5. ሁለቱም የፈርዖን ሕልሞች ፍች ምንድን ነበር?

ሀ- ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት በቀጣዮቹ ሰባት የድርቅ ዓመታት እንደሚዋጡ ተመለከተ።

6. እግዚአብሔር ዮሴፍ ትንሽ ልጅ ሳለ ያሳየውን ሕልሞች እንዴት ፈጸማቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ዮሴፍን በግብፅ ሁሉ ላይ ንጉሥ አደረገው።

7. ያዕቆብ ቤተሰቡን ሁሉ ይዞ ወደ ግብጽ የሄደው ለምንድን ነው?

ሀ- ዮሴፍ በግብፅ ይኖር ስለነበር።

ለ- በግብጽ ብዙ እህል ስለነበር።

- ያዕቆብ ወንዶች ልጆችና መላው ቤተሰቦቻቸው ወደ ግብጽ ሲጓዙ ቁጥራቸው ሰባ ነበር።

ዘጸአት 1፡1-5

1- ቤተ ሰቦቻቸውን ይዘው ከያዕቆብ ጋር ወደ ግብፅ የሄዱት የእስራኤል ልጆች ስሞች እነዚህ ናቸው።

2- ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣

3- ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ብንያም፤

4- ዳን፣ ንፍታሌም፣ ጋድና አሴር።

5- የያዕቆብ ዘር ጠቅላላ ብዛት ሰባ ሲሆን፤ ዮሴፍ ግን ቀደም ብሎ ግብፅ ነበር።

- እግዚአብሔር ለያዕቆብ የሰጠው አዲስ ስም ማን ነበር?

- እስራኤል።

- የአብርሃም የይስሐቅና የያዕቆብ ዘሮች ሁሉም እስራኤል ወይም እስራኤላውያን ተባሉ።

- ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍና ወንድሞቹ እንዲሁም መላው ቤተሰቦቻቸው ለብዙ ዓመታት በግብፅ ኖሩ።

- የራብ ዘመን ካበቃ በኋላ ዮሴፍና ወንድሞቹ በግብፅ መኖር ቀጠሉ።

- አባታቸው ያዕቆብ ከሞተ በኋላም ዮሴፍና ወንድሞቹ በግብፅ መኖር ቀጠሉ።

- በኋላም ዮሴፍና ወንድሞቹ ሞቱ እስራኤላውያንም በግብፅ መኖራቸውን ቀጠሉ።

ዘጸአት 1፡6

6- ከጊዜ በኋላ ዮሴፍና ወንድሞቹ፥ ያም ትውልድ በሙሉ ሞቱ።

- እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ሳይመለሱ ለብዙ ዓመታት በግብፅ በመቆየታቸው፥ ብዙ ሕዝብ ሆኑ።

ዘጸአት 1፡7

7- ይሁን እንጂ እስራኤላውያን እየተዋለዱ በዙ፤ ቁጥራቸው እጅግ ከመጨመሩም የተነሣ የግብፅን ምድር ሞሏት።

- ከብዙ ዓመታት በኋላ የግብፅ ንጉሥ ፈርዖን ሞተ።

- ከዚያም ሌላ ፈርዖን በእርሱ ምትክ ነገሠ።

- አዲሱ ንጉስ እንደ ቀድሞው ደግ አልነበረም።
- አዲሱ ንጉስ በጣም ክፉ ሰው ነበረ።

ዘጸአት 1፡8-11

8- በግብጽም፣ ስለ ዮሴፍ የማያውቅ አዲስ ንጉሥ ነገሠ።
9- እርሱም ሕዝቡን እንዲህ አላቸው፤ «እነሆ፤ እስራኤላውያን በቁጥር በልጠውናል፤ ከእኛም ይልቅ እየበረቱ ነው።
10- ቁጥራቸው እንዳይጨምር፣ ጦርነት ቢነሣ፣ ከጠላቶቻችን ጋር አብረው እንዳይወጉንና ከምድሪቱም ኮብልለው እንዳይሄዱ ዘዴ እንፈልግ።

11- ስለዚህ እያስጨነቁ የግዳጅ ሥራ የሚያሠሯቸውን አሠሪ አለቆች ሾሙባቸው። እስራኤላውያንም ፊቶምና ራምሴ የተባሉ ንብረት ማከማቻ ከተሞችን ለፈርዖን ሠሩለት።

- አዲሱ ንጉስ በእስራኤላውያን ላይ ምን አደረገባቸው?

- እስራኤላውያንን በሙሉ ባሪያዎች አደረጋቸው።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ባሪያዎች ያደረጋቸው ለምን ነበር?

- እስራኤላውያን አገሩን እንዳይወርሱ ስለፈራ ነበር።

- ፈርዖን እስራኤላውያን አገሩን እንዳይወርሱ የፈራው ለምን ነበር?

- እስራኤላውያን እጅግ በዝተው ስለነበር ነው።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ባሪያዎች እንዲያደርጋቸው የመራው ማን ነበር?
- ሰይጣን።

- ሰይጣን እስራኤላውያንን ለማጥፋት የፈለገው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር አዳኝ ከእስራኤላውያን ዘር እንደሚልክ ያውቅ ስለነበር ነው።

- ሰይጣን እግዚአብሔርን ይጠላል።
- ሰይጣን ሰዎችን ሁሉ ይጠላል።

- ሰይጣን እግዚአብሔር ከእስራኤል ዘር አዳኝ እንዲልክ አልፈለገም።

- ሰይጣን አዳኝ መጥቶ ሰዎችን እንዲያድን አልፈለገም።

- ሰይጣን ሁላችሁንም ይጠላል።

- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ቃል እንድትሰሙ አይፈልግም።

- ሰይጣን ሁላችሁም ወደ ዘላለሙ የእሳት ባሕር እንድትጣሉ ይፈልጋል።

- ሰይጣን እስራኤልን ሊያጠፋ ቢፈልግም እንኳ እግዚአብሔር ጠበቃቸው።

- ሰይጣን እስራኤልን ሊያጠፋ ቢፈልግም እንኳ እግዚአብሔር ባረካቸው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የባረካቸው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለሚወዳቸው ነው።

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባውን ቃል የማያጥፍ ስለሆነ ነው።

ዘጸአት 1፡12-14

12- ነገር ግን ባስጨነቋቸው መጠን፣ የእስራኤላውያን ቁጥር በዛ፣ በምድሪቱም እየተስፋፉ ሄዱ፤ ከዚህም የተነሣ ግብፃውያኑ እስራኤላውያንን እጅግ ፈሯቸው፤

13- ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታም ያሠሯቸው ጀመር።

14- ጭቃ በማስቦካት፣ ጡብ በማሠራትና በእርሻም ሁሉ እያስጨነቁ ከባድ ሥራ እንዲሠሩ በማድረግ ሕይወታቸውን አስመረሩ፤ ግብፃውያኑ በሚያሠሯቸው ከባድ ሥራ ሁሉ ፈጽሞ አይራሩላቸውም ነበር።

- ምንም እንኳ ፈርዖን እስራኤላውያንን የበለጠ ቢያስጨንቃቸውም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የበለጠ ባረካቸው።

- ከዚያም አንድ ቀን ሰይጣን ለፈርዖን ሌላ ክፉ አሳብ አቀበለው።

ዘጸአት 1፡15-22

15- የግብፅ ንጉሥ ሲፓራና ፉሐ የተባሉትን ዕብራውያን ሴቶች አዋላጆች እንዲህ አላቸው፤

16- «የዕብራውያንን ሴቶች በማማጫው ድንጋይ ላይ በምታዋልዱበት ጊዜ የሚወለደው ሕፃን ወንድ ከሆነ፣ ግደሉት፤ ሴት ከሆነች ግን፣ በሕይወት ትኑር።

17- አዋላጆቹ ግን እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ የግብፅ ንጉሥ ያዘዛቸውን አልፈጸሙም፤ ወንዶቹን ልጆች በሕይወት እንዲኖሩ ተዉአቸው።

18- ንጉሡም አዋላጆቹን ጠርቶ «ለምንድን ነው ወንዶቹን ልጆች በሕይወት እንዲኖሩ የተዋችኋቸው?» አላቸው።

19- እነርሱም፣ «የዕብራውያን ሴቶች እንደ ግብፃውያን ሴቶች አይደሉም፤ ብርቱዎች ስለ ሆኑ አዋላጆች ከመድረሳቸው በፊት ይወልዳሉ» ሲሉ ለፈርዖን መለሱለት።

20- ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር ለአዋላጆቹ መልካም ሆነላቸው፤ ሕዝቡም በቁጥር እየበዛና እያየለ ሄደ።

21- አዋላጆቹም እግዚአብሔርን በመፍራታቸው፣ ቤተ ሰብ ሰጣቸው።

22- ፈርዖንም፣ «የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ዐባይ ወንዝ ጣሉት። ሴት ልጅ ሁሉ ግን በሕይወት ትኑር» ሲል ሕዝቡን አዘዘ።

- ሰይጣን ለፈርዖን ያቀበለው ሌላው ክፉ አሳብ ምን ነበር?

- ሰይጣን ለፈርዖን ያቀበለው ሌላው ክፉ አሳብ የእስራኤል ወንድ ሕፃናት መገደል አለባቸው የሚል ነበር።

- እግዚአብሔር ሰይጣን እስራኤላውያንን ሊያጠፋ ማቀዱን ያውቅ ነበር?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ሰይጣን እስራኤላውያንን እንዲያጠፋ ፈቀደለት?
- አልፈቀደለትም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ጠበቃቸው።

- እግዚአብሔርም እስራኤላውያንን ከግብጽ ምድር ለማውጣትና ወደ ከነዓን ምድር ለመመለስ አቀደ።

- እግዚአብሔር ሙሴ በተባለ ሰው መሪነት እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ ወደ ከነዓን ለመመለስ ዐቀደ።

- የሙሴ ታሪክ ይህ ነው።

ዘጸአት 2፡ 1-4

1- በዚያን ጊዜ ከሌዊ ነገድ የሆነ አንድ ሰው አንዲት ሌዋዊት ሴት አገባ።

2- እርሷም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ሕፃኑ መልከ መልካም መሆኑን ባየች ጊዜ፣ ሦስት ወር ሸሸገችው።

3- ከዚያ በላይ ልትሸሽገው ባልቻለች ጊዜ ግን፣ የደንገል ቅርጫት ወስዳ፣ በዝፍትና በቅጥራን ለቀለቀችው፤ ሕፃኑንም በውስጡ አስተኝታ

ቅርጫቱን ዐባይ ወንዝ ዳር ቄጤማ መካከል አስቀመጠችው።

4- የሕፃኑም እኅት የሚደርስበትን ነገር ለማወቅ ራቅ ብላ ቆማ ታይ ነበር።

- የሙሴ አባትና እናት በእግዚአብሔር አመኑ።

- የሙሴ አባትና እናት እግዚአብሔር ሕፃኑን እንደሚጠብቀው አመኑ።

- ስለዚህ እግዚአብሔር ሕፃኑ ሙሴን በቅርጫት አድርገው በዓባይ ወንዝ ላይ እንዲያስቀምጡ ጥበብ ሰጣቸው።

- እግዚአብሔር ልጃቸውን ሙሴን ጠብቆታል?

ዘጸአት 2፡5-10

5- በዚህ ጊዜ የፈርዖን ልጅ ልትታጠብ ወደ ዐባይ ወንዝ ወረደች። በምትታጠብበትም ጊዜ ደንገጥሮቿ በወንዙ ዳር ወዲያና ወዲህ ይሉ ነበር። በቄጤማውም መካከል የተቀመጠ ቅርጫት አይታ ከደንገጥሮቿ አንዷን እንድታመጣው ላከቻት።

6- ቅርጫቱን ስትከፍተው ሕፃኑን በውስጡ አየች፣ ያለቅስ ስለ ነበረም አዘነችለትና፣ «ከዕብራውያን ሕፃናት አንዱ መሆን አለበት» አለች።

7- የሕፃኑ እኅት ለፈርዖን ልጅ፣ «ሕፃኑን እያጠባች የምታሳድግልሽ ከዕብራውያን ሴቶች መካከል ሞግዚት ላምጣልሽ?» አለቻት።

8- የፈርዖንም ልጅ፣ «መልካም፣ ሂጂ» አለቻት። ልጅቱም ሄዳ የሕፃኑን እናት ይዛ መጣች።

9- የፈርዖን ልጅ ሴቲቱን «ይህን ሕፃን ወስደሽ እያጠባሽ አሳድጊልኝ፣ ደመወዝ እከፍልሻለሁ» አለቻት። ሴትዮዋም ሕፃኑን ወስዳ አሳደገችው።

10- ሕፃኑም ባደገ ጊዜ፣ ወደ ፈርዖን ልጅ አመጣችው። ልጇም ሆነ፤ እርሷም፣ «ከውኃ አውጥቼዋለሁና» ስትል ስሙን ሙሴ ብላ

ጠራቸው።

- እግዚአብሔር የክፉውን የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን ከሞት እንድትታደገው አደረገ።

- እግዚአብሔር የክፉውን የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን እንድታሳድገው አደረገ።

- ሙሴም ከክፉው ፈርዖንና ከሴት ልጁ ጋር ኖረ።

- እግዚአብሔር የፈርዖን ሴት ልጅ ሙሴን እንድታሳድገው ለምን አደረገ?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሴ መሪነት ከግብፅ ለማወጣት ዐቅዶ ስለነበር ነው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሴ መሪነት ከግብፅ ባርነት ለማወጣት ዐቅዶ ስለነበር ነው።

- እግዚአብሔር ሙሴ በፈርዖን ቤት ምንም ጉዳት እንደማያገኘው ያውቃል።

- እግዚአብሔር ሙሴ በፈርዖን ቤት መጻፍና ማንበብ እንደሚማር ያውቃል።

- እግዚአብሔር ሙሴ በፈርዖን ቤት እስራኤላውያንን ለመምራት የሚያስፈልጉትን ብዙ ነገሮች እንደሚማር ያውቃል።

- ፈርዖን እስራኤላውያንን ሊያጠፋ ፈለገ እግዚአብሔር ግን ጠበቃቸው።

- ሰይጣንና አጋንንቱ ደግሞ እስራኤላውያንን ሊያጠፉ ፈለጉ እግዚአብሔር ግን ጠበቃቸው።

- ሰው የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያስቆም ይችላል?
- አይችልም።

- አጋንንት የአግዚአብሔርን ሥራ ሊያስቆም ይችላል?
- አይችልም።

- ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያስቆም ይችላል?
- አይችልም።

- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነው።

- እግዚአብሔር እስራኤልን ጠበቀ እንዲሁም በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ይጠብቃቸዋል።

- ሙሴ በፈርዖን ቤት ውስጥ አደገ አድጎም ትልቅ ሰው ሆነ።

- አንድ ቀን ሙሴ እስራኤላውያን በባርነት ምን ያህል በመሠቃየት ላይ እንዳሉ ለመመልከት ወጣ።

ዘጸአት 2፡11-14

11- ሙሴ ካደገ በኋላ፣ አንድ ቀን፣ ወገኖቹ ወደሚገኙበት ስፍራ ወጣ፤ በዚያም ተገድደው ከባድ ሥራ ሲሠሩ ተመለከተ። ዕብራዊ ወገኑንም አንድ ግብፃዊ ሲደበድበው አየ።

12- ሙሴም አካባቢውን ቃኝቶ ማንም አለመኖሩን ካረጋገጠ በኋላ፣ ግብፃዊውን ገድሎ አሸዋ ውስጥ ደበቀው።

13- በማግሥቱም በወጣ ጊዜ ሁለት ዕብራውያን እርስ በርሳቸው

ሲጣሉ አየ፤ ጥፋተኛውን፣ «የገዛ ወገንህን የምትመታው ለምንድን ነው?» አለው።

14- ሰውየውም፣ «አንተን በእኛ ላይ ገዥና ዳኛ ማን አደረገህ? ግብፃዊውን እንደ ገደልኸው እኔንም ልትገድለኝ ትፈልጋለህን?» አለው። ሙሴም፣ «ለካስ ያደረግሁት ነገር ታውቆአል» በማለት ፈራ።

- እስራኤላውያን ራሳቸውን ከፈርዖን እጅ ማዳን ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ለማዳን በመሞከር አንድ ግብፃዊ ገደለ።

- ነገር ግን ፈርዖን ሙሴ አንድ ግብፃዊ መግደሉን ደርሶበታል።

- ፈርዖን ምን አደረገ?

ዘጸአት 2፥15

15- ፈርዖን ይህን በሰማ ጊዜ፣ ሙሴን ሊገድለው ፈለገ፤ ሙሴ ግን ከፈርዖን ሸሽቶ ወደ ምድያም ሄደ።

- ፈርዖን ሙሴ አንድ ግብፃዊ መግደሉን ደርሶበታል።
- ስለዚህ ፈርዖን ሙሴን ሊገድለው ፈለገ።

- ሙሴ ፈራ ሸሸም።
- ሙሴ ወደ ምድያም አገር ኮበለለ።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ማዳን ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ለማዳን ሞከረ ነገር ግን አልቻለም።

- እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ማዳን የቻለው ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- ሰዎችን ከሰይጣን እጅ ማዳን የሚችለው ማን ነው?
- እግዚአብሔር።

- እስራኤላውያን የፈርዖን ምርኮኞች እንደ ነበሩ ሁሉ ሁሉም ሰዎች የሰይጣን ምርኮኞች ናቸው።

- እስራኤላውያን ከፈርዖን እጅ ራሳቸውን ማዳን እንዳልቻሉ ሁሉ ሁሉም ሰዎች ከሰይጣን እጅ ራሳቸውን ማዳን አይችሉም።

- ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ ማዳን እንዳልቻለ ሁሉ ማንም ሰው እኛን ከሰይጣን እጅ ማዳን አይችልም።

- እግዚአብሔር ብቻ እስራኤላውያንን ከፈርዖን እጅ እንዳዳነ ሁሉ ሁሉንም ሰው ከሰይጣን እጅ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- በሚቀጥለው ትምህርት ስለ ሙሴ የበለጠ እንማራለን።